የሰ.መ.ቁ. 217855
ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ሥልጣን ወ/ሚካኤል

2. ወ/ሮ ጠጅቱ ሁንዴ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ኦሜጋ ተረዳ

2. አቶ ሸዋንግዛው ኦሜጋ

3. አቶ በለጠ ኦሜጋ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ታህሳስ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 223936 የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 193612 ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪዎች በቅደም ተከተል 1ኛ

፣2ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች፣ በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉት ወ/ሪት ሙሉ ወርቅ አሜጋ እና ወ/ሮ ሸዋዬ ሰይድ በቅደም ተከተል ደግሞ 3ኛ እና 5ኛ ተከሻሶች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ልዩ ስሙ አስኮ ተብሎ ለሚጠራው ሰፈር የተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች ይዞታ የሚያሳየው 275 ካ.ሜ ሲሆን የአመልካቾች ደግሞ 152 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ ነው፣ ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች በቤት ቁጥር 378 ካርታ ላይ ካለው 275 ካ.ሜ ይዞታ ተጨማሪ ከአመልካቾች ይዞታ ስር የሚገኝ 35 ካ.ሜ አላግባብ የያዙ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች ከካርታቸው ውጪ የያዙትን ቦታ በመሃንዲስ ተለክቶ አለግባብ የወሰዱት ተረጋግግጦ እንዲለቁ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች እና የስር 3ኛ ተከሳሽ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ ተጠሪዎች ወደ አመልካቾች ይዞታ 35 ካ.ሜ በመግባት አለመያዛቸውን በመግለጽ የአመልካቾች ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚዎችን በብይን ውድቅ ያደረገ ሲሆን በፍሬ ነገር ላይ ደግሞ የኮልፌ ቀራንዩ ክፍለ ከተማ ይዞታ አስተዳደር ሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ዴስክ ስለጉዳዩ አጣርቶ ምላሽ እንዲሰጥበት አድርጐ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ አመልካቾች ያቀረቡት ማስረጃ እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ጽ/ቤት በሴሪ.ቁ.048821 በካርታ ቁጥር 014/ወዝ01/924/1757/1 ለ1ኛ አመልካች 152 ካ.ሜ በሆነው ይዞታ ላይ የሰጠው ካርታ ላይ ተቃራኒ ማስረጃ አልቀረበም፣ ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች ወደ አመልካቾች ይዞታ በስተደቡብ አቅጣጫ 26 ካ.ሜ የሚሆን ቦታ አጥረው እንደያዙ በሚመለከተው አካል ተረጋግጧል፣ አመልካቾች ለክርክር መነሽ የሆነውን መሬት ከተጠሪዎች እና ከስር ተከሳሾች በግዥ ስለማግኘታቸው አልተካደም፣ ግራ ቀኙ የያዙት ይዞታ በካርታ ላይ ካለው ያነሰ እንደሆነ በሚመለከተው አካል ተረጋግጧል፣ ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች ከይዞታቸው ላይ 82 ካ.ሜ ያህል እንደተቀነሰ የሚመለከው አካል ያመነ በመሆኑ በምን አግባብ ወደማን ይዞታ ተቀላቅሎ ተቀነሰብን የሚለውን ነጥብ በተመለከተ ክስ መስርቶ ከማስወሰን በቀር ይህንን መከራከሪያ ፍርድ ቤቱ ያልተቀበለው መሆኑን፣ተጠሪዎች እና የስር ተከሳሾች በስተደቡብ በኩል አጥረው የያዙትን 26 ካ.ሜ አጥሩን አንስተው ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ በማለት ተወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዋናው ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማለታቸውን እና አመልካቾች ደግሞ በወጪና ኪሣራ ላይ መስቀልኛ ይግባኝ አቅርበው የነበረ ሲሆን ፍርድ ቤቱም መዝገቡን አጣምሮ ተመልክቶ ስለጉዳዩ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የመሬት የይዞታ አስተዳደር ጉዳዩን አጣርቶ ምላሽ እንዲሰጥ ካደገ በኋላ ተጠሪዎች በተጨባጭ የያዙት ይዞታ በካርታ ከተሰጣቸው ይዞታ ያነሰ መሆኑ ተረጋግጧል፣ በተጠሪዎች ታጥረው የሚገኘው ይዞታ በካርታ ለአመልካቾች  የተሰጠ እና የካርታ መደራረብ መኖሩ ተረጋግጦ ባለበት ተጠሪዎች የአመልካቾችን ይዞታ ገፍተው ይዘዋል የሚባልበት የህግ አግባብ የለም፣ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በስተደቡብ በኩል አጥረው የያዙት 26 ካ.ሜ ቦታ ለአመልካቾች ለቀው እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሳኔ ማስረጃን መሰረት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያላደረገ እና ተጠሪዎች የአመልካቾችን ቦታ ገፍተው መያዝ አለመያዛቸው በአግባቡ ሳያጣራ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ ሽሮ ተጠሪዎች ለቀው የሚያስረክቡት ይዞታ የለም፤ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የተሻረ በመሆኑ የአመልካቾች በወጪና ኪሣራ ላይ አቅርበውት የነበረው መስቀለኛ ይግባኝ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካቾች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን አመልካቾች ታህሳስ 12 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክፍለ ከተማው ከሰጠው ማስረጃ ውጪ የሰጡት ውሳኔ እና ትዕዛዝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 22 መ.ቁ. 122595 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጥስ ነው፤ በመሆኑም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በግራ ቀኙ ከተደረገው ክርክር ማስረጃ ምንም እንኳን በግራ ቀኙ ካርታ ላይ መደራረብ የሚታይ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱም ሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ባጣሩት መሰረት የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት አጣርቶ ያልያዘውን ተጠሪዎች ወደ አመልካቾች ይዞታ አልፈው በመግባት መያዛቸው ተረጋግጦ ባለበት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለአመልካቾች ሊለቅ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ሲሽር ይህ ውሳኔ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተቀባይነት ያገኘበት አግባብ ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪዎች መጋቢት 16 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ተጠሪዎች ወሰን ገፍተው የአመልካቾችን ይዞታ ይዘዋል የሚል ምላሽ አልሰጠም፤ ተጠሪዎች ወደ አመልካቾች ይዞታ በስተደቡብ በኩል 26 ካ.ሜ አልፈን አለመያዛችን ተረጋግጧል፤ አመልካቾች በተጠሪዎች እጅ እና ይዞታ ስር በሚገኘው መሬት ከህግ እና ደንብ ውጪ የተሰራ ካርታ ይዘው መገኘታቸው ብቻ የንብረቱ ባለቤት እንደማያደርጋቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጽ 9 መ.ቁ. 36320 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፤ የተጠሪዎች ካርታ ከአመልካቾች ካርታ ቀድሞ የተሰጠ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት የተጠሪዎች ካርታ በአመልካቾች ካርታ ላይ የበላይነት አለው፤ ተጠሪዎች አሁን በተጨባጭ ከያዝነው የይዞታ ስፋት በካርታ ላይ ከተመዘገበው የይዞታ ስፋት ያነሰ ስለመሆኑ በባለሙያ ተረጋግጧል፤ በመሆኑም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዞ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ልውውጥ በዚህ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም የቀረበውን አቤቱታ በስር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ከተጠረገው አጠቃላይ ክርክር እና ከተሰጡ ውሣኔዎች እንዲሁም ከማስቀረቢያ ነጥቡ አንፃር ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በአመልካቾች ቀርቦ የነበረው ክርክር ተጠሪዎች ከይዞታችን ያለአግባብ 35 ካ.ሜ. ገፍተው የያዙ በመሆኑ እንዲለቁ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች በበኩላቸው ገፍተው የያዙት ይዞታ እንደሌለ በመግለጽ ክሱ ውድቅ ይደረግልን ሲሉ መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አስተዳደሩን ጠይቆ ባገኘው መረጃ መሠረት የካርታ መደራረብ ያለ መሆኑ ተገልጾለታል፡፡

ከአጠቃላይ ክርክሩ ይዘት የሚዋሰኑ ይዞታዎች መካከል ባለ ይዞታ ክርክር ምክንያት የካርታ መደራረብ መኖሩ ከተረጋገጠ ከካርታ መደራረብ አኳያ ጉዳዩ ተመርምሮ ሊወሰን የሚችልበትን አግባብ በስር ፍ/ቤቶች በአግባቡ ተመርምሮ የመወሰኑን አግባብነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

አንድ የፍትሐብሄር ክርክር የሚመራው እና ጭብጡም የሚመሰረተው ከሣሽ የሆነው ተከራካሪ ወገን በክስ አቤቱታው ላይ የገለፃቸውን ፍሬ ነገሮች እና ተከሣሽ የሆነው ወገን በመከላከያ መልሱ ላይ የገለፃቸውን ፍሬ ነገሮች ክሱን ለመከላከል ያስችለኛል በማለት በማለት ያቀረበውን ማስረጃዎችን እንዲሁም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 241መሠረት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሲሰማ ያገኘውን ፍሬ ጉዳዩችን በማገናዘብ ስለመሆኑ ስለጭብጥ አመሠራረት የሚደነግጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከቁ. 246-248 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች ከይዞታችን ውስጥ 35 ካ.ሜ. የሆነውን ተጠሪዎች ገፍተው ይዘውብናል በሚል የሚከራከሩ ሲሆን በስር ፍ/ቤት በተደረገ ማጣራት በደቡብ በኩል ተጠሪዎች ወደ አመልካቾች ይዞታ 26 ካ.ሜ. ገፍተው ይዘዋል በሚል ተረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ባደረገው ማጣራት ደግሞ የካርታ መደራረብ መኖሩ በሚመለከተው አካል ተረጋግጧል፡፡ በሁለቱም ፍ/ቤቶች በተደረገው ማጣራት ግራ ቀኙ ይዘው የሚገኙት ይዞታ ጥርት ባለመልኩ በያዙት ካርታ ይዞታ መጠን ይዞታውን ይዘው የሚገኙ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡

የካርታ መደራረብ ያለ በሆነ ጊዜ ካርታው እንዴት አንዱ በአንዱ ይዞታ ላይ ተደርቦ እንደተሰጠ፣ ለምን መደራረቡ እንደተፈጠረ፣ በይዞታው ተፈጥሮ አኳያ የማን ካርታ የማንኛው ይዞታ ላይ እንደተደረበ እና እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል ተጣርቶ ግራ ቀኙን የሚያከራክረው ጉዳይ መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤት ካርታ መደራረብ ስላለ ብቻ አንዱ አንዱን ገፍቶ ይዟል ሊባል የማይቻል ነው በሚል

ውሣኔውን መሻሩና ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የስር ፍ/ቤቶች የፈፀሙብትን ስህተት ማረም ሲገባው ማጽናቱ ተገቢ አይደለም ብለን ተከታዩን በአብላጩ ድምፅ ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1) የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 193612 ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 223936 በ24/06/12 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 78580 በ22/02/2011 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2) የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በውሣኔ የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሃተታው ተገለንው መሠረት የካርታ መደራረቡን ምክንያት ካርታ በመደረቡ ሊሰጥ የሚችለውን ውሣኔ የሚመለከተው አካል ተገቢ ማብራሪያ እንዲሰጥ በማድረግ እና ግራ ቀኙ አስቀድሞ ያቀረቡትን ማስረጃ አብሮ በመመርመርና በማጣራት ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ እንዲወስን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 343/1/ መሠረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡

3) በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ የወጣ ወጪ ካለ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

<u>መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

# የሃሣብ ልዩነት

እኛ በሶስተኛ እና አራተኛው ተራ ቁጥር ስማችን የተጠቀሰው የችሎቱ ዳኞች አብላጫው ድምፅ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት በመመለስ በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማን በመሆኑ ያለንን የልዩነት ሀሳብ እንደሚከተለው አስፍረናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኸው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ከፍስ/ስ/ህ/ቁ 136፣ 137.272 እና 345 ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረት የሚሆንን ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳያጣሩ መወሰን አግባብ ባለመሆኑ በክርክሩ የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ባልሆኑበት ጊዜ እና እነዚህን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰን ፍትህን የሚያዛባ ከሆነ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲያቀርብ መታዘዝ አለበት፡፡ / በሰበር መዝገብ ቁጥር 72980 እና 22603 በተመሳሳይ ጉዳይ የተሰጡ አስገዳጅ ውሳኔዎችን ይመለከቷል፡፡/ በዚህ አግባብ አከራካሪው ጉዳይ በስር ፍ/ቤት ተጣርቶ እንዲወሰን ሊመለስ የሚችለው ከላይ እንደተመለከተው ከግራ ቀኙ ክርክር አንፃር የተያዙና ሊያዙ የሚገባቸው ጭብጦች በአግባቡ ተጣርተው ያልተወሰኑ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ግራቀኙ ከሚከራከሩበት ይዞታ አንፃር የግራ ቀኙን ካርታ በተመለከተ መደራረብ መኖር አለመኖሩ በአግባቡ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ ሲሆን የኮ/ቀ/ክ/ከ/መሬት ልማት ማኔጅመንት ፅ/ቤት በ 05/05/2012 ዓ.ም ጉዳዩን በይግባኝ ለተመለከተው ሌፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በላከው ማብራሪያ የግራቀኙ ካርታ መደራረብ ያለው መሆኑን የተደራረበውም 68 ካሜ መሆኑን ማረጋገጡን የገለፀ ሲሆን መደረቡ የተፈጠረውም የአመልካች ካርታ ሲሰራ በ 1997 ዓ.ም አየር ካርታ ላይ የሚታየውን ቤት መሰረት በማድረግ በሽንሻኖ ማስተካከያ በመሆኑና በመስክ ልኬት ስለመከናወኑ የሚያሳይ ማረጋገጫ ባለመኖሩ መሆኑን በዚህ ምክንያትም በተጠሪዎችም ታጥሮ የሚገኘው ይዞታ በአመልካቾች ካርታ ውስጥ ተካትቶ ሊሰጥ መቻሉን የገለፀ ሲሆን የኮ/ቀ/ክ/ከ/የይ/አስ/የሽ/ጊ/አ/ፐ/ዴስክ በ22/09/2010 ዓ.ም ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ምላሽ መደራረብ የተፈጠረው የመስክ ልኬት ሳይደረግ በጂአይ ኤስ አየር ካርታን መሰረት በማድረግ ካርታው በመዘጋጀቱ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች መረጋገጡ የካርታ መደራረቡ የተፈጠረው ካርታው የተሰጠው መሬቱን በአግባቡ ለመያዙ ሳያረጋግጥ ሂደቱ በመፈፀሙ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤቶች መዝገብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ፅ/ቤት በተጨማሪም በሰጠው ምላሽ የተጠሪዎች ካርታ በ 18/12/08 ዓ.ም የአመልካቾች ካርታ በ 11/06/2008 ዓ.ም ከመዘጋጀቱ 6 ወር ያህል በፊት የተዘጋጀ መሆኑን በማመልከት ቅድሚያ የሚሰጠው ቀድሞ መብት ለተፈጠረለት ሰው መሆኑን በሚያመለክት መልኩ መልስ መስጠቱን የስር ፍርድቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

በመሠረቱ የካርታ መደራረብ ሲፈጠር ክፍተቱን የሚሞላ ህግ ባለመኖሩ በአሰራር የዳበረው መሬቱን ለያዘው ሰው ወይም ቀድሞ መብት ለተፈጠረለት ሰው ቅድሚያ መስጠት ተቋማቱ በአማራጭነት የሚከተሏቸው ምርጫዎች ሲሆኑ አሁን በያዝነው ጉዳይ ከላይ እንደተመለከተው ካርታው ሲዘጋጅ አከራካሪው ይዞታ በተጠሪዎች እጅ መኖሩ እንዲሁም አስቀድሞ መብት የተፈጠረውም ለተጠሪዎች

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሆኑ በአሰራር በዳበሩት ሁለቱም አማራጮች ቢሆን ተጠሪዎች በአከራካሪው ይዞታ ላይ የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ከላይ ከተመለከቱት አማራጮች አንዱን በመውሰድ የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪዎች ለአመል78 ካቾች ለቀው የሚያስረክቡት ይዞታ የለም በማለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠጠው ውሳኔ ከውጤት አንፃር ሊፀና ይገባ ነበር በማለት ከስራ ባልደረባዎቻችን በሃሳብ ተለይተናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም